# የአሜሪካ ድምጽ ከዶክተር ሐይሉ ጋር የተለዋወጠው የታሪክ ምጸት

የቀይሽብር ብቻ ሰለባወች ናቸው? ስሙ ጠበበ፣ ለምን ቀይሽብር አላችሁት? ቀይሽብር ብቻ ለምን ሆነ በጎኑ ነጭሽብርም ነበረ በማለት አቶ አዲሱ አበበ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋዜጠኛ ለቀይሽብር ማህበር ተወካይ አቶ ይጥናን ይጠይቃል።

ዶክተር ሐይሉ አርያ የቀድሞው የኢሰፓ አባል፤ ቀጥሎም የልደቱ ፓርቲ ኢዴፓ መስራች ሲመልሱ ሽብሩ ሁለት መልክ ያለው ነው ያም ነጭ ሽብር የሚባል ነበር በዚያም ወጣት ልጆች የመንግስት አባላትን ሽጉጥ ታጥቀው ገድለዋል ይላሉ። ይህ አበባላቸው በጠያቂው አዲሱ አበበ ጸሐፊው ያልታወቀውን መጽሀፍ በመጥቀስ አቶ ይጥናን ነጭሽብር የሚባል እንደነበር የዚያን ሰለባወችም መታሰብ ነበረባቸው ጠቧል በማለት ያፋጥጣል።

ለመሆኑ ቀይሽብርን ማን አወጀው? ነጭ ሽብርስ ያወጀ የፖለቲካ ድርጅት ነበር? ዶክተሩም ሆነ ጋዜጠኛው በዚያ የተካሄደ ትግል ገዳይና

ሟች፣ ወንጀለኛና ወንጀሉ የተፈጸመባቸው ዜጎች ባንድ ይቁሙ፣ በአንድ ይፈረዱ አይነት አባባል ይዘው መጠዋል። ለዶክተሩ አዲስ አይደም። ከቬኦኤው ጋዜጠኛ አፍ ግን ይህን ለመጀመሪያ መስማቴ ነው። በእርግጥ እስከዚህ ሰአት ድረስ ትልቅ ክብር ነበረኝ፣ ግን በምን መስፈርት ሙታን ከገዳያቸው ጋር ይፈረዱ እንዳለ አልገባህ ስላለኝ ያን አንድ ትውልድን የመተረ ሽብር ያቀነባበረው፣ ያካሄደው አንድ መንግስትና በስሩ የተሰባሰቡ አድር ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው። ቀዩ ሽብር ጋዜጠኛው እንዳለው ተቃሎ የሚቀርብ አይደለም። ብዙ ጉድ ያለው ነው። በሁሉም ታላላቅ ከተሞች፣ በቀበሌወችና በገበሬ ማህበራት ጭምር የማጎሪያ ካምፖች ተቋቁመው ነበር። እነዚያ ካምፖች አዲስ ቤት ተቀይሶ ወይም የራሳቸው የሆነ በረት ተሰርቶ ሳይሆን በተግባር ላይ የነበሩ የትላልቅ ድርጅቶችን፣ ትምህርት ቤቶችን ወይም ሆቴሎችን ወደማጎሪያ በመቀየር የተመሰረቱ ናቸው። በነዚያ ማጎሪያ ቦታወች የማሰቃያ ማህከሎች ተዘጋጅተው ሌት ከቀን የተቀለቡ ደብዳቢወች ተመድበው ዜጎችን እንደበግ አርደዋል። ይህ የተጋነነ አይደለም የሆነ ነው። እኔም

አንዱ ስለነበርሁ ማለት ነው። ማሰቃያወች ዜጋን በመግረፍ፣ በቢላ በመተልተል፣ በኮረንቲ በማቃጠል፣ በወንድ ብልት የሞላ ጠርሙስ በማሰር፣ በሴት ማህጸን የጋለ ብረት በመስደድ እንዲለፈልፉ ማድረግ ነው። ከዚህ ስቃይ የተረፉ የተጻፈላቸውን ፈርመዋል። በቀጣዩም አምነዋል በማለት በቀይሽብር ምልክት ተገለው በየመንገዱ ተጥለዋል።

በነገራችን ላይ በግርፊያውና ከማሰቃያ ክፍል ሳይወጡ ያለቁት ዜጎች ቀላል አልነበሩም። ዶክተሩና ጋዜጠኛው የሚነግሩን እነዚያ አሰቃዮችና ገዳዮች፣ ወንጀሉ ከተፈጸመባቸው ተገራፊወች ብሎም ከሟቾቹ ጋር አብረው ይቁሙ ነው።፡ወይ ምጸት።

ለሁሉም ይህ ክርክርና መልስ ሰጭወች በአንድ በኩል ጠያቂውና ጥያቄው በሌላ በኩል አስገራሚ የሆኑ ከሁሉም በዳይን፣ ወንጀለኛን፣ መከላከል ወይም ሟች ያውም ያለህግ በሽብር በግፍ የሞተን መውቀስ መክሰስን የያዘ አስቀያሚ ልውውጥ ነበር። ሐቅ የጎደለውን ያክል ሰሚን

ዳግም የሚያስጨንቅ ዳግም ዱላ ብለው ይቀላል። ባገራችን ይህ የመጀመሪያ እንዳልሆነ ደጋግሞ ታሪክ አሳይቶናል። የቬኦኤውም ጥያቄና መልስ ( በሰው ቁስል እንጨት ቢሰዱበት....) እንደተባለው ከዚያ ተርፈው የአእምሮ ቁስል ላልጠገገላቸው ዳግም ግምት ያላስገባ ጨካኝ ልውውጥ (እንጨት እንጨት) የሚል ነበር። ለነገሩ ይህች አገር ወንጀለኛ የሚፈራረቅባት፣ በጎ አሳቢወች፣ መልካም ነገር አድራጊወች የተሰደዱባት፣ የሞቱባት፣ በግፍ የተፈረዱባት ናት። ጀግናን ገሎ መፎከር ዛሬ አይደለም የተጀመረ። በቀደሙት ዘመናት ላገር ሲሉ ለነጻነት ሲሉ በዱር በገደል አምስትአ አመት ኖረው የፈረጠጡትን ፡ወዳገራቸው እንዲመለሱ የግር መርገጫ መሬት የሰጡት በላይ ዘለቀ፣ ነጋሽ በዛብህ ጠላት በሰማይ በምድር ሞክሮ ተቸንፎ የተዋቸውን፣ በተጋድሎቸው ከስደት የመለሷቸው መኳንንትና መሳፍት ገድለዋቸዋል። ይህ የታሪክ ምጸት ዛሬ በአሜሪካው ድምጽ ራዲዮ ዘጋቢና በኢሰፓ የቀድሞ አባል ቢደገም አዲስ አይደለም ለማለት ነው።

ቀይሽብር በአዋጅ አልወጣም ይላል አዲሱ፡- መልሱን ወዲያው አግኝቷል ሆኖም አንድ ጋዜጠኛ በእድሜው ያየውን የሰማውን ለመካድ ለምን ተገደደ?  ሌላ ቢቀር ከስቱዲዮ ወጣ ብሎ ወይም ወደአንዱ የዲሲ ምግብ ቤት ጎራ ብሎ ሁለት ሶስት ሰው ማናገር እንዴት ይሳነዋል? ያልታወቀ ሰው መጽሀፍ፣ ስምየለሽ ለበለው መጥቀሱ እንደጋዜጠኛ አግባብ አልነበረም። አወ ዛሬ ከእስር የሚወጡ፣ ለዚህ በዳይ ጠባብ መንግስት መተያያ ሲሉ አሁንም ጳጳት ያልነካቸው ጸሐፊወች ታሪክን ገልብጠው ለመጻፍ ከጅለዋል አርገዋልም።

ጠያቂው እንደ ኢሰፓ ወንጀለኞች አሁንም ይሁነኝ ብሎ ካልገፋበት ቀይሽብር ብሎ ማን አወጀው ነጭ ሽብርስ በማን የሚለውን የሚስተው አይመስለኝም። የዚያ ሰለባ የነበሩ፣ ለዘመናት በእስር ኖረው የወጡ፣ አካለ ስንኩን በሽህወች የሚቆጠሩ ዛሬም በህይወት አሉ። የልጆቻቸውን ህልፈት ያልተረዱ ወላጆችም እዲሁ። የፈለገው እውነትን ማወቅ ከሆነ እስካሁን አፋቸው ከተሸበቡት አንዱን ማቅረብ ይችል ነበር ባይ ነኝ።

ያጽልመትና ወንጀሉን ፈጻሚወች ለዚህ ላለንበት ሁኔታ ትልቁን ድርሻ አበርካች ናቸው። አቶ አዲሱ ቀይሽብር የለም ለማለት ምን አዳዳው? የተተፋ አይመለስ ይባላል። ታሪክ እንደሰው እሩህ ሩህ ልትሆን አትችልም። ታሪክን ገልብጦ ለማንበብ ወይም ለመስራት መሞከርም እንዲሁ ከባድ አደጋ ነው። ያውም አገር፣ ህዝብ፣ ሌላው አለም በሚያዳምጠው መገልገያ።

ዛሬም የተቃዋሚ መሪ በመሆናቸው በተስፋ የምንጠብቃቸው ዶክተር ይህን አይነት በአንድ ትውልድ ላይ የተፈጸመ በደል እና ወንጀል ለመካድ ምን አስመረጣቸው? የሚታገሉት መልሰው ያነን ጽልመት ለማምጣት ይሆን። ያሳዝናል።

<u>ቀዩ ሽብር በእርጥም ታውጇል</u>

መስከረም ወር ቀኑን በትክክል ባላውቅም 1970 እ ኤ አ መንግስቱ ሐይለማሪያም አቢዮታዊ ጥሪ በሚል ህዝብ በአብዮት አደባባይ ሰብስቦ ሦስት ጠርሙሶች በደም የተሞሉ ከመሬት በማጋጨት እየወረወረ መፈክር ሰጠ። መፈክሩ ሞት ለጸረ አብዮተኛ፣ ሞት ለኢሕአፓ፣ ቀይ ሽብር ይፋፋም የሚሉ መፈክሮች ነበሩ።

ከዚህ እለት በቀደመ አያሌ ወራቶች ማለትም ከ1968 እ ኤ አ አጋማሽ ጀምሮ የነጻ እርምጃ የሚሉትን ባዋጅ ያልወጣ በመኢሶን፣ እና ከደርግ ባበሩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር በመሆን የተጠረጠሩ ግለሰቦችን በተለይም መሀከለኛ እድሜ 18 የሚሆኑ ወጣቶችን ሌት ከቤት ቤት በመዛዋወር ወጣት አለበት ከሚሉት ለፍተሻ በሚል በመግባት ከተኙበት እየወሰዱ መግደል ይፋ ቀዩ ሽብር እስከታወጀበት ቀን ቀጥሏል። ለዚህ አቶ አዲሱ አበበም ሆነ ዶክተር ሐይሉ አርያ ያለምንም ፍርድ የተገደሉ ወይም ተገለው የተገኙ ሰወችን የሚያመላክት ዜና በዚያን ጊዜ ይወጡ ከነበሩት አዲስ ዘመን ኢትዮጵያን ሔራልድ እላታዊ ጋዜጦች እና የዛሬይቱ

ኢትዮጵያ ሳምንታዊ ጋዜጣ መመልከት ይቻላል። ያም በይፋ የተነገሩትን በጋዜጦች የዘገቡትን ለማየት ከተፈለገ ማለት ነው። ሐምሌ 1968 እ.ኤ.አ የአየር ሐይሉ ኮሎኔል ሲሳይ ሐብቴ፣ ኮሎኔል ኪሮስ የእድገት በህብረት ዘመቻ መምሪያ ዋና ሐላፊ ከሌሎች ነጋዴወች ጋር (የበርበሬ ሻጥር) ብሎ ካሰራቸው ጋር ተገለዋል። ያን ሙሉ ክረምት ግድያው በከፋ ሁናቴ ቀጥሎ መስከረም 1/1969 በእለተ ቅድሴዋንስ አዲስ የመንጥረው አዋጅ ተደመጠ። የአዋጁ እርእስ ከብብትህ ያለውን እሳት ታውቃለህ በሚል የወጣና በሰላም ሲንቀሳቀስ በቆየ የፖለቲካ ድርጅት ላይ የተነጣጠረ አዋጅ ነበር። ይህ አዋጅ ኢሕአፓ ሆኖ የተጠረጠረን ሁሉ ለመግደል በመንግስት ለአስታጠቃቸው የገበሬ፣ የቀበሌ ማህበራትና ለከተማ ፖሊሶች የሚፈቅድ አዋጅ ነበር። ይህንን ዶክተሩም ሆነ የሾአኤው ዘጋቢ አይስቱትም።

በቀጣይ 12 ወራት ማለትም ከመስከረም 69-70 አመተምህረት የነጻው እርምጃ ቀጥሎ በመስከረም 70 ዓ.ም መንግስቱ ሶስት በደም የተሞሉ

ጠርሙሶችን አብዮት አደባባይ በህዝብ ፊት በመወርወር በአይነቱ ልዩ የሆነውን ዘመቻ ጀመረ። በዚያ ዘመቻ አንድ ትውልድ ተመትሯል። እናቶች ልጆቻቸውን ሳያዩ በዋሉበት ቀርተዋል። የልጅ እሬሳን በየመንገዱ ማግኘት የተለመድ ሆነ አገሪቱ ዘግናኝ በሆነ የሰው ልጆች ሊቀበሉት በማይችል ጽልመት ውስጥ ገባች። አቶ አዲሱ የት ነበር አሳፋሪው ታሪካዊ ወንጀል ሲካሄድ?

ደርግ ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይደመሰሳል አለ እንጅ፣ ነጭ ሽብር ያወጀ የፖለቲካ ድርጅት አልነበረም። በዶክተሩ አመላለስ የእናቶች የማታ ኡኡታ ሽብር ነበር ካሉት። ያም ቢሆን እራሱን የቻለ ታሪካዊ አመጣጥ ነበረው። የተጨነቁ የተጠበቡ እናቶች ለሁለት አመታት የቀጠለውን የሌሊት ቤት ፍተሻ በመቃወም ልጆቻቸውን ከገዳይ ቀበሌወችና ከደርግ እስኳድ ለመከላከል ያደርጉት የነበር የድረሱልን ጥሪ ነበር። ያም ሆኖ ማትረፍ አልተቻለም።

ዶክተሩም ጋዜጠኛውም ለነጭ ሽብር ሰለባወች ጭምር ሀውልት ይቁም አልን እንጅ፣ በቀይሽብር ለተገደሉ አታቁሙ አላልንም በሚል ምጸት ሀሳቦቻቸውን አጠቃለዋል። አቶ አዲሱ የጋበዘውን እንግዳ ጊዜ ላለመስጠት ያደርግ የነበረው ጥድፊያ ከሁሉም በላይ አሳዝኖኛል። የዚያ ትውልድ አባላት የቀዮ ሽብር ሰለባወች ዛሬም እያለን፣ የልጆቻቸውን እሬሳ ያላዩ ወይም ያልቀበሩ እናቶች ለዘመናት በጉንጉን ገመድ ወገባቸውን እንዳሰሩ የኖሩት አሁንም ገና ሳያልቁ እንዴት ሆኖ እንዲህ አይን ያወጣ ሚችን ዳግም ገዳይ ድንፋታ በተከበረ የራዲዮ ፕሮግራም ሊሰማ ቻለ?

ለማጠቃለል፡- ታሪክ ጨካኝ ናት። ምህረት አይኖራትም። ትናንት በሆነው ጸጸት የለሽ ወንጀለኞች ዛሬም በየስደት አገር ሆነው ከንስሀ ይልቅ ዳግም ግዳይን ቢመኙ አይገርምም።ግን ታሪክን ገልብጠው ሊጽፉ በምንም አይቻላቸውም። አንድ ትውልድን መትሮ አሁንም ማሾፍ ቋሚን

ያሳዝናል። ካልጠበቁት በኩል የተዛባ ያስተሳሰብ ፍርደገምድልነት በማየቴ ከልክ ያለፈ ሐዘን ተሰምቶኛል።

መንግስቱ ሞሴ አስረስ

ከዳላስ፣ ቴክሳስ